# መንግሥት ለአውሮፓ ኮሚሽን ፕሬዚዳንት ቢሮ ጠንካራ ደብዳቤ ፃፈ

እ.ኤ.አ ኦክቶበር 24/2006 የኢትዮጵያ መንግሥት በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በኩል ብራሰልስ ለሚገኘው የአውሮፓ ህብረት ኮሚሽን ፕሬዚዳንት ቢሮ ጠንክር ያለ ደብዳቤ መፃፉን ምንጮች ገለፁ::

የደብዳቤው ትኩረትም የሠሌዳ ቁጥሯ ኮድ 89-019 በሆነችው መኪና የኮሚሽኑ የኢትዮጵያ ልዑክ ጽ/ቤት ሠራተኞች የሆኑት ሚ/ር ቦርን ዮሐንሰን እና ሚ/ር ኤንሪክ ሶርጂ የተባሉት በሞያሌ በኩል በህግ የሚፈለጉ ኢትዮጵያውያን ለማስወጣት ጥረት ሲያደርጉ እጅ ከፍንድ መያዛቸው ላይ ያተኮረ ነው::

በህገ ወጥ መንገድ ከአገር እንዲወጡ በኮሚሽኑ ሠራተኞች የተደረገው ሙከራ ለማስወጣት የሞከሯቸውን ግለሰችን በህግ የመፈለጋቸው ነገር እንኳ ወደ ጎን ቢተው ድርጊቱ በራሱ ከሁለቱ የኮሚሽኑ ተቀጣሪዎች ተግባርና መብት ጋር የሚጣረስ ወንጀል መሆኑን መንግሥት በደብዳቤው ላይ ጠቅሷል:: ይህን ተግባር በመፈፀምም ግለሰቦቹ ዓለም አቀፍ ህግን፣ የኢትዮጵያን ህግ፣ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና ደህንነትን የተፃረረ ድርጊት መፈፀም እንደሆነ ከዚህም በተጨማሪ በኢትዮጵያ የዲፕሎማቲክ ታሪክ ውስጥ እምብዛም ተፈፅሞ የማያጋጥምና በአውሮፓ ኮሚሽን የኢትዮጵያ ጽ/ቤት ባልደረቦችም በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል ያለውን፣ ሊኖር የሚገባውን መተማመንና ጥሩ ግንኙ ነት የሚጎዳ መሆኑን በደብዳቤው ላይ ተገልጿል:: እነዚህ ሁለት ግለሰቦች ያላቸው የሥራ ደረጃ የአስተዳደርና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ከመሆኑ አንፃር የዲፕሎማቶቹን መብትና ግንኙነት በሚያስቀምጠው የቬና ስምምነት መሠረት በፈፀሙት ተግባር በኢትዮጵያ ህግ መሠረት ፍርድ ቤት ቀርበው ተገቢውን እርምጃ ከመውሰድ የሚያግድና ከመጠየቅ ነፃ የሚያደርግ የዲፕሎማቲክ ደረጃ እንደሌላቸው ሆኖም ግን የኢትዮጵያ መንግሥት በአውሮፓ ህብረትና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን ለረጅም ጊዜ የቆየ ወዳጅነትና ግንኙነት በማየት ይህን መሰሉን እርምጃ አልወሰደም:: ይልቁንም ብዙ ወሬና ጋጋታ ሳይፈጠር በኮሚሽኑ የኢትዮጵያ ኃላፊ ለሆኑት ሁኔታውን በማሳወቅ ሁለቱ

ሠራተኞች ክብራቸውንና ሰብዓዊ መብታቸውን በጠበቀ መልኩ ከአገር እንዲወጡ ማድረጉን ጠቅሷል፡፡

ይህንን ያተተው ደብዳቤ የተፈፀመውን ድርጊት ሙሉ በሙሉ አጣርቶ ለዘላቂ መፍትሄ ለመብቃት አስፈላጊ የሆነውን ከጅምሩም እነዚህ ሁለት ግለሰቦች ወደ ሞያሌ ለምን ዓላማና በምን ምክንያት እንደተጓዙ የኮሚሽኑ የኢትዮጵያ ጽ/ቤት ኃላፊ በፅሁፍ እንዲያብራሩለት ጥያቄ ማቅረቡን፣ ሆኖም ግን ተገቢውን ወቅታዊ ምላሽ ይህን ደብዳቤ ከተፃፈበት ኦክቶበር 24/2006 ድረስ እንዳላገኘ ገልጾ በኮሚሽኑ የአዲስ አበባ ጽ/ቤትና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል ያለው ግንኙነት በዚህ መሰል ተገቢ ያልሆኑ ተግባሮችና አካሄዶች የተነሳ ከተወሰነ ጊዜ አንስቶ እየተበላሸ መምጣቱን ጠቁሞ፤ ዘላቂ መፍትሄን ለማምጣት የሚያስችል ትኩረትና እርምት እንደሚሻ አስታውቋል፡፡

በዚህ ሁሉ ደረጃ የግለሰቦች በተለይም በኮሚሽኑ የኢትዮጵያ ጽ/ቤት በኃላፊነት ደረጃ ላይ የሚገኙ መሪዎች በሥራቸው የሚገኙትን ሠራተኞች የገንቢና ህጋዊ ግንኙነትን የሚያጎላበት አርአያና ምሳሌ በመሆን የሚጫወቱት ሚና የማይናቅ መሆኑን መንግሥት አስምሮበታል፡፡

በኢትዮጵያና ብራሰልስ በሚገኘው የአውሮፓ ኮሚሽን መካከል ያለው የጠበቀና ለረጅም ጊዜ የዘለቀ መልካም ግንኙነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል የኢትዮጵያ መንግሥት የሚጠበቅበትን ሁሉ እንደወትሮው እንደሚያደርግ በደብዳቤው ላይ ተገልጿል፡፡